ቁ.2
(ጥር 2015)

ነፃነትና እኩልነት ፓርቲ

የነፃነት ዐግ

በነፃነትና እኩልነት ፓርቲ የሚዘጋጅ የፓርቲው ልሳን

ሶስተኛው የፖለቲካ መስመር

(Third way politics)

ቁ.2
(ጥር 2015)

የነፃነት ዋግ

የንፃነትና እኩልነት ፓርቲ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና የትግል ስልቶች የሚተነተኑበት የንድፍ ሀሳብ እና አማራጭ የፖሊሲ ሀሳቦች የሚዳሰሱበት የፓርቲው ወርሃዊ መጽሔት ነው።

አዘጋጅ፡ የነእፓ ህዝብ ግንኙነት
ስልክ፡ 011 381 0080
ፋክስ፡ 011 381 0065
ኢሜይል፡ fepeditorial@gmail.com
ድረገጽ፡ www.fepethiopia.com

03

ሶስተኛው የፖለቲካ መስመር

05

የኢትዮጵያ የፖለቲካ አጀንዳ/ ትርክት ማስፋት

07

ትምህርት መር ብሄራዊ የልማት ስትራቴጂ

10

የስድስተኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ስድስት ተሞክሮዎች

12


ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስር

ሶስተኛው የፖለቲካ መስመር

(Third way politics)

ሶስተኛው የፖለቲካ አስተሳሰብ የግራ እና የቀኝ የፖለቲካ ፍልስፍናዎችን በማስታረቅ የተፈጠረ ቅይጥ እና መካከለኛ የፖለቲካ አስተሳሰብ ነው። ሶስተኛው የፖለቲካ አስተሳሰብ ምንም እንኳን የተለያዩ የፖለቲካ እሳቤዎች ውህድ ቢሆንም የሚከተላቸው የፖሊሲ አቅጣጫዎች አልፎ አልፎ የግራ ወይም የቀኝ ፖለቲካ ተጽእኖ ይታይበታል። ከዚህ አንጻር የሶስተኛው መንገድ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ወደ ግራ ያሚያጋድሉ ሲሆን የማህበራዊ ፖሊሲዎቹ ደግሞ ከቀኝ ዘመም ፖለቲካ የተጨለፉ ናቸው። ሶስተኛ መንገድ ፖለቲካ በይዘቱ "የመካከለኛ ወይም ሚዛናዊ" የፖለቲካ አስተሳሰብ ጋር ይመሳሰላል።

> **ከዚህ አንጻር የሶስተኛው መንገድ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ወደ ግራ ያሚያጋድሉ ሲሆን የማህበራዊ ፖሊሲዎቹ ደግሞ ከቀኝ ዘመም ፖለቲካ የተጨለፉ ናቸው።**

የሶስተኛው መስመር ፈጣሪዎች እና አቀንቃኞች በተለይ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኃላ እየጨመረ የመጣውን የመንግስት በኢኮኖሚ ውስጥ ጣልቃ ገብነት የተቃወሙ የፖለቲካ መሪዎች እና ምሁራን ናቸው። የሶስተኛው የፖለቲካ መስመር ደጋፊዎች ከፍተኛ የመንግስት ጣልቃ ገብነትን ከሚያቀነቅነው "የሶሻሊስት ስርአት" እና በኢ-ፍትሀዊነት ከሚወቀሰው "የካፒታሊዝም ስርአት" በማዳቀል እና በመቀመር የፈጠሩትን የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ውቅር "ሶስተኛው መንገድ" በማለት ሰይመውታል።

ሶስተኛው መንገድ (Third way) የሚለው ሀረግ ላለፉት ጥቂት ምእተ አመታት የተለያዩ የፖለቲካ ፍልስፍናዎችን እና ሀሳቦችን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ይውል እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ። አስተሳሰቡ በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ ተራማጅ የፖለቲካ አስተሳሰብ እንከተላለን በሚሉ የፖለቲካ ኃይሎች ከርእዮተ ዓለም ወደ ፖሊሲ ተቀይሮ ተተግብሯል።

የአሜሪካ ፕሬዝዳንት የነበሩት ቢል ክሊንተን እኤአ በ1992 የምርጫ ዘመቻ ወቅት ባደረጉት ንግግር ሶስተኛውን የፖለቲካ አስተሳሰብ እንዲህ ሲሉ ገልጸውታል። "የሶስተኛው መንገድ ከሊበራል ካፒታሊዝም የሚለይ በነጻ ገበያ ኢኮኖሚ እና ዴሞክራሲ ጠንካራ እምነት ያለው፣ ለኢኮኖሚ እድገት ለግለሰብ የሀሳብ ነጻነት፣ ምርታማነት እና የሀብት ማመንጨት ልዩ ትኩረት የሚሰጥ፣ ማህበራዊ ፍትህን የሚያቀነቅን እና መንግስት ለዚህ አላማ መሳካት የአንበሳውን ድርሻ ሊወስድ እንደሚገባ በጽኑ የሚያምን የፖለቲካ አስተሳሰብ ነው" በሌላ በኩል የሶስተኛ መንገድ ንድፈ ሀሳብ ተመራማሪ እና ጸሃፊ የሆነው አንቶኒ ጊደን ይህ ፍልስፍና አክራሪ የሶሻሊዝም እሳቤዎችን እና ልቅ እና ገደብ የሌሽ የሆነውን የኒዎ-ሊበራል አስተሳሰቦችን የሚቃወም እና በሁለቱ ጽንፎች መካከል ወርቃማውን አማካኝ መስመር የሚከተል የፖለቲካ አስተሳሰብ እንደሆነ ይገልጻል።

እኤአ በ1990 መጨረሻ ሶስተኛ የፖለቲካ አስተሳሰብ የሚከተሉ መንግስታት በአውሮፓ እና በሌሎች የአለማችን ክፍሎች በስልጣን ላይ ነበሩ። አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ጣልያን፣ ብራዚል እንዲሁም አንዳንድ የአሲያ ሀጋራት እንደ ምሳሌ ይጠቀሳሉ። በዚያን ዘመን "ሶስተኛው መንገድ" ተብሎ የሚጠራው የፖለቲካ ፍልስፍና ሰፊ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ነበረው። ይህ አስተሳሰብ ከ ተ ለ መ ደ ው መንግስት መር የሶሻሊስት አስተሳሰብ እንዲሁም ነጻ ገበያን እና ልቅ ነጻ ኢኮኖሚን

> **የሶስተኛው የፖለቲካ መስመር ደጋፊዎች ከፍተኛ የመንግስት ጣልቃ ገብነትን ከሚያቀነቅነው "የሶሻሊስት ስርአት" እና በኢ-ፍትሀዊነት ከሚወቀሰው "የካፒታሊዝም ስርአት" በማዳቀል እና በመቀመር የፈጠሩትን የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ውቅር "ሶስተኛው መንገድ" በማለት ሰይመውታል።**

ከሚያራምደው የካፒታሊዝም ፍልስፍና በተለየ መልኩ ማህበራዊ ፍትህን፣ ፍትሀዊ እና አካታች የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ይከተላል።

የሶስተኛው የፖለቲካ መስመር ደጋፊ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚከተሉትን ማህበረ ኢኮኖሚ እና ፖለቲካዊ ፖሊሲዎችን በሙተግበር ይታወቃሉ፤ ዜጎች ፍትሀዊ የትምህርት እና ስልጠና

እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታን በመፍጠር በማህበረሰቡ ውስጥ ፍትሀዊ የሀብት እና የገቢ እድሎች እንዲፈጠር ማድረግ፤ የመንግስት በጀት (ገቢ እና ወጪ) የተመጣጠነ እንዲሆን በማድረግ መንግስታት ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት በሌላቸው ፕሮጀክቶች ከሚሰበስቡት ገቢ በላይ ወጪ በማውጣት የበጀት ጉድለት እንዳይፈጥሩ እና የማክሮ ኢኮኖሚ መፋለስ እንዳይፈጠር መምከር። ያልተማከለ የመንግስት ስልጣን (Decentralization of power) በልማት ሰራዎች የመንግስት እና የግል ዘርፍ በሽርክና መስራት፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል በብዛት እና በጥራት ማፍራት እና አካባቢን መጠበቅ የዚህ አስተሳሰብ ሌሎች መገለጫዎች ናቸው።

> **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የሚከተለው የሶስተኛ መንገድ አስተሳሰብ ለሀገራዊ አንድነት ልዩ ዋጋ ይሰጣል፣ ብሄር እና ቋንቋን ጨምሮ ሌሎች ተፈጥሯዊ ልዩነቶችን ያከብራል።**

የሶስተኛው የፖለቲካ አስተሳሰብ በዓለም ዙሪያ በተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፣ በአብዛኛው የሶሻል ዲሞክራት እና ማህበራዊ ፍትህን የሚያቀነቅኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች የዚህ እሳቤ ተከታይ ናቸው። ምንም እንኳን ከላይ የተገለጹት ፖሊሲዎች የሶስተኛው ፖለቲካ አስተሳሰብ መገለጫዎች ቢሆኑም፣ አስተሳሰቡ በሁሉም ሀገራት አንድ ወጥ የሆነ ትርጓሜ እና አተገባበር የለውም። በዚህም ምክንያት የሶስተኛው መንገድ ፖለቲካን የሚከተሉ በተለይ በአውሮፓ እና አሜሪካ የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ልዩነት ይታይበታል።

በርካታ የሀገር መሪዎችም የሶስተኛውን አማራጭ በማቀንቀን እና በስራ ላይ በማዋል ይታወቃሉ። ከእነዚህ ታዋቂ መሪዎች መካከል አሜሪካን ኢ.ኢ.አ ከ1993 እስከ 2001 የመሩት ፕሬዝዳንት ቢል ክሊንተን አንዱ ሲሆኑ የዚህ አስተሳሰብ ቀንደኛ ደጋፊ ነበሩ። የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚንስትር ሆነው ያገለገሉት ቶኒ ብሌር ሌላው የዚህ አስተሳሰብ አፍቃሪ እና ደቀ መዝሙር የነበሩ ሲሆን በስልጣን ዘመናቸው የውጭ ጉዳይን ጨምሮ በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች "ሶስተኛ መንገድ" በመባል የሚያወቁ ፖሊሲዎችን ይተገብሩ እንደነበር ይገለጻል።

በተመሳሳይ ሀገረ እንግሊዝን እአአ ከ1957 እስከ 1963 ያስተዳደሩት ጠቅላይ ሚንስትር ሀሮድ ማክሚላን መንግስታቸው የሚከተለው ፖሊሲ ሶስተኛ የፖለቲካ አስተሳሰብን እንደሆነ "መካከለኛው መንገድ" በሚል ስያሜ ባዘጋጁት መጽሀፋቸው ውስጥ ገልጸዋል። የቀድሞዎቹ የጀርመኑ መራሄ መንግስት (ቻንስለር) ገርሀርድ ሽሮደር፣ የጣልያኑ ጠቅላይ ሚንስቴር ሮማኖ ፕሮዲ የዚሕ ሀሳብ አራማጅ እንደነበሩ በስልጣን ዘመናቸው ይከተሉ የነበሩትን ፖሊሲዎች ያጠኑ ምሁራን ይመሰክራሉ። በአህጉራችን አፍሪካ የቀድሞው የሊቢያ ፕሬዝደንት ሞአመር ጋዳፊ እና የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝዳንት ታቡ ሚቤኪ የሶስተኛው መንገድ ፖለቲካ ፖሊሲዎችን ይከተሉ እንደነበር ዜና መዋእላቸው ያስረዳል።

የሶስተኛው ፖለቲካ ብዙ ደጋፊዎች እና አድናቂዎች እንዳሉት ሁሉ አስተሳሰቡን የሚተቹ በርካቶች ናቸው። የኮሚኒስት የፖለቲካ ርእዮተ ዓለም አቀንቃኝ ፖለቲከኞች እና ምሁራን አስተሳሰቡ የኒዮ ሊበራላ እሳቤን የሚከተል ነው በማለት አጥብቀው ይኮንኑታል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የሶስተኛው መንገድ

በሀገራችን የሶስተኛ ፖለቲካ መንገድ ከሚከተሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች አንዱ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ (ነእፓ) ነው። ነእፓ የዓለም የፖለቲካ ፍልስፍና እና ታሪክን ፣ ከሀገራችንን የፖለቲካ፣ የማህበረሰብ፣ የአስተዳደር ታሪክ እና ልማድ ጋር አዛምዶ እና አዋዶ በሚዛናዊነት እና ምክንያታዊነት ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ርእዮተ ዓለም ይከተላል። ነእፓ "ሚዛናዊ ሊበራሊዝም" ብሎ የሰየመው የፖለቲካ ፍልስፍና "የግራ ዘመም" እና "ቀኝ ዘመም" የፖለቲካ ፍልስፍናዎችን እንዲሁም የነጻነት (Freedom) እና የእኩልነት (Equality) ጽንሰ ሀሳቦችን ለሀገራችን በሚስማማ መልኩ አስታርቆ በሀገራችን ዘላቂ እና አስተማማኝ ሰላም፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እድገት፣ ሀገራዊ አንድነት እና መግባባትን እውን ለማድረግ የፖለቲካ ፕሮግራሙን ቀርጿል። ይህ መንገድ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲን በኢትዮጵያ የሶስተኛው የፖለቲካ መስመርን አስተሳሰብ አራማጅ ያደርገዋል።

የነእፓ የሶስተኛ መንገድ ፖለቲካ በአውሮፓ እና ሌሎች ሀገራት ከተለመደው የግራ እና ቀኝ ፍልስፍና በተጨማሪ ሌሎች ሀገር በቀል መገለጫዎች ያሉት ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ እና ዋነኛው የሀገራችን ፖለቲካ ማጠንጠኛ ከሆነው የማንነት ፖለቲካ አንጻር ነእፓ የሚከተለው ሚዛናዊ አስተሳሰብ ነው። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ላለፈው ግማሽ ምእተ አመት በላይ በሀገራችን ከተንሰራፉት ሁለት ዋልታ-ረገጥ የፖለቲካ ርእዮተ ዓለሞች ማለትም ጠርዝ የረገጠ የብሄር ፖለቲካ እና "በአንድነት" ስም ለብዝሀነት በቂ እና እውነተኛ እውቅና ለመስጠት ከሚውተረተር የፓለቲካ መስመር በተለየ መልኩ አንድነትን ከብዝሀነት ጋር አጣጥሞ የሚጓዝ የፖለቲካ አስተሳሰብ ውልድ ነው።

ነእፓ የግለሰብ እና የቡድን መብቶች አንዱ ከሌላው ጋር ሳይጋጭ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ማስኬድ ይቻላል ብሎ ያምናል። ነእፓ የሚከተለው ይህ የፖለቲካ አስተሳሰብ እና የፖሊሲ ማእቀፍ ፓርቲውን ከሌሎች በሀገራችን ከነበሩ እና ካሉ የፖለቲካ ኃይሎች የተለየ ያደርገዋል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የሚከተለው የሶስተኛ መንገድ አስተሳሰብ ለሀገራዊ አንድነት ልዩ ዋጋ ይሰጣል፣ ብሄር እና ቋንቋን ጨምሮ ሌሎች ተፈጥሯዊ ልዩነቶችን ያከብራል።

የነእፓ ሶስተኛው መንገድ የፖለቲካ ፍልስፍና በአንድ በኩል የግዛት አንድነቷ የተከበረ ሁሉም ዜጎች በፈለጉበት የሀገራችን ክፍል በነጻነት መኖር፣ መስራት፣ ሀብት ማፍራት ወዘተ የሚያስችላቸው ጠንካራ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ እንዲገነባ የሚፈቅድ ሲሆን በሌላ በኩል የብሄር፣ የቋንቋ፣ የሀይማኖት፣ የባህል ወዘተ ልዩነቶች በእኩልነት እንዲከበሩ በማድረግ መላው የሀገራችን ህዝቦች ልዩነታቸውን አክብረው በመፈቃቀር እና በመፈቃቀድ በጋራ የሚኖሩባን ሀገር ለመገንባት ያስችላል።

ነእፓ የሚከተለው ይህ ሚዛናዊ የፖለቲካ አስተሳሰብ ሀገራችን ዛሬ ላይ ካለችበት ዘርፈ ብዙ እና ውስብስብ ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና ማህበራዊ ችግሮች እንድትላቀቅ አማራጭ እና አዋጭ የፖለቲካ መስመር ነው ብሎ ያምናል። ነእፓ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ የሀገራችን ፖለቲካ ዋልታ ረገጥ ከሆኑ አስተሳሰቦች ተላቆ ሚዛናዊ አስተሳሰብን እንዲከተል ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ የቆየ ሲሆን፣ ወደፊትም ይህንኑ ጥረቱን አጠናክሮ በመቀጠም ሶስተኛው የፖለቲካ መስመር በሀገራችን እውን እንዲሆን ይሰራል።

●●●

የኢትዮጵያ የፖለቲካ አጀንዳ/ትርክት ማስፋት

ከ1950 መባቻ በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንደተጀመረ የሚነገርለት የለውጥ እንቅስቃሴ ገና ከጅምሩ ግራ ዘመም በሆነ የማርክሲስት ሌኒንስት ርእዮተ ዓለም ላይ ተመስርቶ የማንነትና የብሄር ጥያቄ የሀገራችን የፖለቲካ ትግል መሰረት እና ዋነኛው መገለጫ ሆኖ ዛሬ ላይ ደርሷል። በወቅቱ የነበሩ የተማሪ እንቅስቃሴ እና የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች በሀገራችን ለረዥም ግዜ የቆዩ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ጭቆናዎችን ሲተነትኑ በግዜው ከነበሩት በርካታ የፖለቲካ ጥያቄዎች የማንነት ጥያቄ ተለይቶ እና ገዝፎ ወጣ። በዚያ ወቅት በማንነት ጥያቄ ዙሪያ በርካታ ጽሁፎችና መጣጥፎች የተጻፉ ሲሆን የዋለልኝ መኮንን "On the Question of Nationalities in Ethiopia" በግምባር ቀደምትነት ይጠቀሳል።

በዚህም ምክንያት የብሄር ጥያቄ የአብዛኛዎቹ የወቅቱ የፖለቲካ ድርጅቶች ዋነኛው እና ብቸኛው የፖለቲካ ጥያቄ ለመሆን ቻለ።በተለያየ ግዜ ተመስርተው የከሰሙ ወይም እስከ አሁን የፖለቲካ ትግል በማካሄድ ላይ የሚገኙ የፖለቲካ ኃይሎች የብሄር ጥያቄን ዋነኛው የፖለቲካ አጀንዳቸው ማጠንጠኛ አድርገው ተነሱ። ከንጉሱ ዘመን ማብቂያ ጀምሮ በደርግ የመጀመሪያ ጥቂት ዓመታት በርካታ የብሄር እና ብሄረሰብ ነጻ አውጪ ድርጅቶች በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች ተመስርተው አንዳንዶቹ ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል፣ ሌሎቹ በትጥቅ ትግል የሀገራችን ፖለቲካ መሰረታዊ ችግር ያሉትን የብሄር ጭቆና ለማስወገድ መንቀሳቀስ ጀመሩ።

የዘውዳዊው አገዛዝ ተወግዶ በምትኩ ወታደራዊ ደርግ ስልጣን በተቆጣጠረ ማግስት በሁሉም የሀገራችን ክፍል የተቋቋሙት የፖለቲካ ድርጅቶች አብዛኞቹ ዋነኛው የፖለቲካ አጀንዳቸው በማንነት ጥያቄ ላይ የሚያጠነጥን ነበር። የደርግን አምባገነናዊ ስርአት በትጠቅ ትግል የተዋጉት እና ያሸነፉት ኃላም ግንባር ፈጥረው ሀገሪቱን ለሀያ ሰባት ዓመታት የመሩት የገዢው ፓርቲ አባል ድርጅቶች ሁሉም ራሳቸውን የብሄር ነጻ አውጭ ግንባር አድርገው የተደራጁ ኃይሎች ነበሩ።

በተለያየ ደረጃ ብሄር ተኮር ፖለቲካ ከሚያቀነቅኑ የፖለቲካ ኃይሎች በተቃራኒ የቆሙ እና "የህብረ-ብሄር" ወይም "የዜግነት" ፖለቲካን እናራምዳለን የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ሙሉ አቅማቸውን የብሄር ፖለቲካን በመቃወም አለፍ ሲልም የብሄር ፖለቲካን አምርረው በማውገዝና እውቅና በመንፈግ በሌላ ጽንፍ ላይ ቆመው በተለምዶ "አሀዳዊ" ፖለቲካን ያራምዳሉ።የብሄር እና ህብረ ብሄር ፖለቲካ አንዱ ለሌላው በስጋትነት እየቀረበ እና ሁለቱም የፖለቲካ ጎራዎች ራሳቸውን ለማጠናከር የሌላውን ችግር አጉልቶ በማሳየት የሀገራችን ፖለቲካ ከማንነት ጉዳይ ፈቅ እንዳይል የበኩላቸውን አስተዋጾ አድርገዋል።

> **የብሄር እና ህብረ ብሄር ፖለቲካ አንዱ ለሌላው በስጋትነት እየቀረበ እና ሁለቱም የፖለቲካ ጎራዎች ራሳቸውን ለማጠናከር የሌላውን ችግር አጉልቶ በማሳየት የሀገራችን ፖለቲካ ከማንነት ጉዳይ ፈቅ እንዳይል የበኩላቸውን አስተዋጾ አድርገዋል።**

የማንነት ፖለቲካ ለአንዳዶች ለሀገራችን ሰላም፣ እኩልነት እና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ወሳኝ ሆኖ ሲቀርብ ሌሎቻችን በማንነት ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ አደረጃጀት የውድቀት፣ የግጭትና የመበተን አደጋ ምንጭ ሆኖ ይታያል።ሁለቱን የፖለቲካ አስተሳሰቦች ሊያስታርቅ የሚችል ሶስተኛ ወይም መካከለኛ መስመር በብዙዎች ሲቀነቀን አይስተዋልም።

ሲጠቃለል የብሄር እና የማንነት ጥያቄ ባለፉት 60 አመታት የሀገራችን ፖለቲካ ምሰሶና ማገር፣ ጣራና ግድግዳ ሆኖ የቆየ ሲሆን የኢትዮጵያ ፖለቲካ እና የማንነት ጥያቄ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ሆነዋል።

የበርካታ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መኖሪያ ለሆነችው ሀገራችን የብሄር ጥያቄ ከዋና ዋና የፖለቲካ ጥያቄዎች አንዱ መሆኑ የማይጠበቅ አይደለም። በተለይም ማንነትን መሰረት ያደረገ አድሎና ጭቆና በስፋት ተፈጽሟል ተብሎ በብዙዎች በሚታመንባት ሀገር ዜጎች ብሄርን ወይም ቋንቋን መሰረት አድርገው መደራጀታቸው እና መታገላቸው የሚያስገርም አይደለም። ከ1983 ጀምሮ ለሀያ ሰባት አመታት በኢህአዴግ መራሹ የሀገራችን የፖለቲካ ስርአት ፖለቲካችን ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል ሁኔታ የብሄር ፖለቲካ ሆኗል። የፖለቲካ ፓርቲዎች መነሻ እና መድረሻ ፣ አጀንዳ እና ትርክት፣ የምርጫ ማኔፌስቶ እና ፕሮፓጋንዳ ወዘተ ባብዛኛው ብሄርን፣ ማንነትን

እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥን ሆኗል። የማንነት ጥያቄ ከፍተኛ ደረጃ በደረሰባት ሀገራችን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ሳይቀሩ የብሄር ድባብ ያንዣበበባቸው ሆነዋል።

በሀገራችን የብሄር ጥያቄ ዋነኛው እና ብቸኛው የፖለቲካ አጀንዳ መሆኑ ሀገራችንን እና ህዝባችንን ትልቅ ዋጋ አስከፍሏል። በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች የሚከሰቱ ግጭቶች መንስኤያቸው በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ከማንነት ጋር የተያያዙ ናቸው። ለሀገራችን ዴሞክራሲያዊ አንድነት የተሻለ ነው ተብሎ የሚታመነው የፌዴራል ስርአት ባለፉት ሁለት አስርተ አመታት ተግባራዊ የተደረገበት አግባብ የብሄር ጥያቄ ይበልጥ እንዲጦዝ እና ብሄር-ተኮር ግጭቶች ይበልጥ እንዲባባሱ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ ተንቀሳቅሶ መስራት፣ መማር ወይም መኖር አስቸጋሪ ሆኗል።የህዝቦች የአብሮነት እና የወንድማማችነት

> **ለሀገራችን ዴሞክራሲያዊ አንድነት የተሻለ ነው ተብሎ የሚታመነው የፌዴራል ስርአት ባለፉት ሁለት አስርተ አመታት ተግባራዊ የተደረገበት አግባብ የብሄር ጥያቄ ይበልጥ እንዲጦዝ እና ብሄር-ተኮር ግጭቶች ይበልጥ እንዲባባሱ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል።**

ስሜት እጅጉን ተቀዛቅዞ የሲጋት ድባብ በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች ነግሷል። ከአራት አመታት በፊት በሀገራችን የተጀመረው የለውጥ ሂደት ውስጥ የተስተዋሉ የአመራር ግድፈቶች እና የፖለቲካ ስህተቶች ማንነትን መሰረት ያደረጉ ግጭቶች ከፋኖ እንዲባባሱ አድርጓል።
የማንነት ጥያቄ ዋነኛው የፖለቲካ አጀንዳ በሆነባት ሀገራችን ዘርፈ ብዙ እና ውስብስብ ማህበራዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ ችግሮች ተንሰራፍተዋል።ከአለም እጅግ ድሀ ሀገሮች አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያ ህልውናዋን ጭምር የሚፈታተኑ፤ ዘር፣ ቋንቋ፣ ብሄር፣ ሀይማኖት እና ቀለም ሳይለዩ የሁሉም የሀገራችን ህዝቦች ዘመን ተሻጋሪ ችግሮች ተደራርበውባታል። የማንነት ጥያቄ ብቻውን ተለይቶ ይህን ያክል መስፋፋቱ ለሀገራችን ሰላም፣ ልማትና ህልውና እጅግ አሳሳቢ የሆኑ ሌሎች በርካታ ጉዳዮች ትኩረት እንዳያገኙ አድርጓል።

በሀገራችን አራቱም ማእዘን የሚኖሩ ገበሬዎች፣ አርብቶ አደሮች፣ ሴቶች፣ ህጻናት፣ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ ተማሪዎች ወዘተ መሰረታዊ ችግሮቻቸው ተመሳሳይ ነው-ድህነት፣ በሽታ፣ ርሀብ፣ ስራ አጥነት። የትምህርት፣ ጤና፣ የንጹህ መጠጥ ውሀ፣ ትራንስፖርት፣ ልብስና መጠለያ፣ በቂ ምግብ፣ ሰላም እና ደህንነት የመላው ሀገራችን ህዝቦች የዘመናት ህልሞች ናቸው። በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ተማሪዎች እና ወላጆች ጥራት ያለው ትምህርት በተመጣጣኝ ዋጋ ይሻሉ። በአስር ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ገበሬዎች ምርጥ ዘር ማዳበሪያ፣ የግብርና ግብአቶችና ዘመናዊ ሙያ የሚያገኙበት ስልጠና ይሻሉ። ከአመት አመት እየተባባሰ የመጣው የትራንስፖርት ችግር የዜጎች

> **የማንነት ጥያቄ ብቻውን ተለይቶ ይህን ያክል መስፋፋቱ ለሀገራችን ሰላም፣ ልማትና ህልውና እጅግ አሳሳቢ የሆኑ ሌሎች በርካታ ጉዳዮች ትኩረት እንዳያገኙ አድርጓል።**

መሰረታዊ ጥያቄ ቢሆንም ችግሩን ለመፍታት በቂ የፖሊሲ ውይይት ሲካሄድ አይስተዋልም። በከተሞች ውስጥ የትራንስፖርት አገልግሎት ለማግኘት የሚጠብቁ ረዣዥም ሰልፎችን ማየት በጣም የተለመደ ትእይንት ሆኗል።
ልጓም ያጣው የዋጋ ግሽበት እና የኑሮ ውድነት የዜጎችን ህይወት ከፋኝ አመሰቃቅሎታል። ላለፉት አስርተ አመታት ኢ-ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ እና መረን በለቀቀ ሙስና የተበላሸው የሀገራችን ኢኮኖሚ በአንድ በኩል በአለም ተወዳዳሪ ቢሊየነሮችን ሲፈጥር በሌላ በኩል በሚሊዮን የሚቆጠሩ የድሀ ድሀዎችን ቁጥር ወልዷል። ኢትዮጵያውያን ከሁልም የሀገራችን ክፍሎች፣ ከሁልም ብሄር እና ሀይማኖት ባህር ማዶ ይሰደዳሉ፣ ይሞታሉ። ሆኖም ችግራቸው ሀገራዊ አጀንዳ ሆኖ ዘላቂ መፍትሄ ሊያስገኝ የሚችል ስራ ሲሰራ እምብዛም አይታይም። በሀገራችን አራቱም ማእዘን የሚኖሩና ከሀገራችን ህዝብ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ወጣቶች ዋና ችግራቸው ስራ አጥነት ሲሆን ወጣቶቻችንን ላልተፈለገ ማህበራዊ፣ ስነልቦናዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ከመዳረግ ባሻገር የህልውና ጉዳይ ለመሆን በቅቷል።
በጠረፋማ እና ቆላማው የሀገራችን ክፍል የሚኖሩ አርብቶ አደሮች ካሉበት እጅግ አስከፊ የኑሮ ውጣውረድ የሚታደጋቸው የፖሊሲ አማራጮችን በአፋጣኝ የሚሹ ቢሆንም ጉዳዮቻቸው በሀገራችን ፖለቲከኞች ለአፍታም ሲወሳ አይሰማም። ከሀገራችን የቆዳ ስፋት 60% የሚሆነው የአርብቶ አደር ማህበረሰቦችን የሚኖሩባቸው አካባቢዎች መሆኑን ልብ ይሏል። የአካባቢ ጥበቃ፣ የደን መመናመን፣ በርሀማነት የመሳሰሉ ዓለም አቀፋዊ አጀንዳዎች ከቁብ የሚቆጥራቸው የለም።
ሁሉም የሀገራችን ህዝቦች ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ጋር በሰላም፣ በወንድማማችነት፣ በአንድነት፣ በመቻቻል፣ በፍቅር መኖርን ይሻሉ። ይሁን እንጂ የሁሉንም የሀገራችን ህዝቦች የጋራ ተጠቃሚነት ሊያረጋግጡ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ የመስራት ፖለቲካዊ ባህል እና ታሪክ የለንም።
በማንነት ፖለቲካ ብቻ ላይ ማተኮራችን ከሌሎች አህጉራዊና ዓለምአቀፍ ይዘት ካላቸው ጉዳዮች እንድንገለል አድርጎናል። በፍጥነት በማደግ ላይ ባለው ሉላዊነት የተነሳ የአፍሪካ እና የዓለም ምጣኔ ሀብትና ግንኙነቶች ይበልጥ እየተቆራኙ እና እየተወሳሰቡ የመጡ ሲሆን በዚህ ፈርጀ ብዙ ዓለም ዓቀፍ ግንኙነት ውስጥ ጥቅማችንን አስጠብቀን ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችሉ የፖሊሲ አማራጮች ላይ በቂ ትኩረት አላደረግንም። በአካባቢያዊ እና አህጉራዊ የንግድ፣ የባህል እና ፖለቲካ ትስስር ውስጥ ዜጎች በቂ እውቀትና ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችሉ የፖሊሲ አማራጮች ዙሪያ ውይይቶች ሲካሄዱ አይታይም።
ቀደምት ኢትዮጵያዊያን ሀገራዊ እና አለምዓቀፋዊ ሁኔታዎች ታሳቢ ያደረጉ የፖለቲካ አጀንዳዎች ላይ ታግለው አልፈዋል። ከ “ያ ትውልድ” የምንወስደውን መልካም የትግል ተሞክሮ ወስደን ለሀገራችንና ላለንበት ዘመን የሚመጥን አጀንዳ መቅረጽ “የዚህ ትውልድ” ግዴታ ነው። የፖለቲካ ድርጅቶች፣ አክቲቪስቶች፣ የሚዲያ ባለሙያዎች ወዘተ የሀገራችን ፖለቲካ አጀንዳ አድማሱ እንዲሰፋ ትኩረት የተነሳቸው ጉዳዮች በቂ ትኩረት እንዲሰጣቸው ሰፊ ስራ መስራት ይጠበቅባቸዋል።

> **ከ “ያ ትውልድ” የምንወስደውን መልካም የትግል ተሞክሮ ወስደን ለሀገራችንና ላለንበት ዘመን የሚመጥን አጀንዳ መቅረጽ “የዚህ ትውልድ” ግዴታ ነው።**

የሀገራችን ፖለቲካ አልፋ እና አሜጋ የሆነው የማንነት ፖለቲካ አድማስ እንዲሰፋ እና ለዜጎች ኑሮ መሻሻል መሰረት የሆኑ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ትኩረት እንዲሰጣቸው ማስቻል እጅግ አስፈላጊ ነው። ባህልን በተለይም የፖለቲካ ባህልን መቀየር ረዥም ግዜ እና ሰፊ ስራ የሚጠይቅም ቢሆንም በአንድ ወቅት ሊጀመር የግድ ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ የፖለቲካ አጀንዳ እና ትርክት ለግማሽ ምእተ አመት ከተቸነከረበት የማንነት ፖለቲካ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተላቆ የሁሉም ዜጎች መሰረታዊ ችግር ይሆኑትን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግሮች ለመፍታት የሀገራችን የፖለቲካ አውድ ሊሰፋ ይገባል እንላለን።

●●●

ትምህርት መር ብሄራዊ የልማት ስትራቴጂ

ትምህርት፣ እውቀት እና ጥበብ ታሪክ

የሰው ልጅ በምድር ላይ መኖር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ራሱን እና አካባቢውን ለማወቅ ሲተጋ ኖሯል። ሰውን ከሌሎች ፍጡራን ከሚለዩት ጉዳዮች አንዱ እና ዋነኛው መመራመር፣ መጠየቅ፣ ማሰላሰል፣ ማወቅና እውቀትን ማከማቸት መቻሉ ነው። በአለም ላይ ሁሉም ስልጣኔዎች ለትምህርት እና ምርምር ትልቅ ዋጋ ሰጥተዋል። ሁሉም ኃይማኖቶችና ባህሎች ለትምህርት የሚሰጡት ዋጋ እጅግ ከፍተኛ ነው። የቀደምት ስልጣኔ መፍለቂያ እንደሆኑ ከሚጠቀሱት የባቢሎን እና የሱመር ስልጣኔዎች ጀምሮ የህንድ፣ የቻይና፣ የግሪክ፣ የሮማ እንዲሁም በአፍሪካ የግብጽ እና ቲምቡክቱ ስልጣኔዎች ሁሉም መሰረታቸው ትምህርት፣ እውቀት እና ጥበብ ነው።

> ትምህርት ዕውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት የተሰኙ ሶስት የተለያዩ ግን የማይነጣጠሉ አንጓዎች አሉት።

በ18ኛው ክፍለ ዘመን በአውሮፓ የጀመረው የኢንዱስትሪ አብዮት የትምህርት እና የእውቀት ትሩፋት ነው። የመረጃ ዘመን ተብሎ የሚታወቀው ያለንበት የ21ኛው ክፍለ ዘመን በፍጥነት እያደገ የመጣው የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ውጤት ነው። ለትምህርት እና ለእውቀት የተሻለ ዋጋ የሰጡ፣ ጥናት እና ምርምር ላይ ትኩረት ያደረጉ ሃገራት የሰለጠኑ ተብለው በሁሉም መስክ ዓለምን ይመራሉ። የአለማችን ኃያላን ሀገራት ወታደራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና ፖለቲካዊ ኃይል መሰረቱ በእውቀት ላይ የቆመ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ነው። በአለም ላይ "ያደጉ" እና "በማደግ ላይ ያሉ" ተብለው ለሁለት ጎራ ከተከፈሉ ሀገሮች ጀርባ ያለው ሚስጥር ትምህርት ነው።

የትምህርት ትሩፋቶች

ትምህርት ዕውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት የተሰኙ ሶስት የተለያዩ ግን የማይነጣጠሉ አንጓዎች አሉት። ዕውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት ሶስቱ የስልጣኔ ማዕዘናት በመባልም ይታወቃሉ። ትምህርት ለአንድ ሰው እውቀት እና ክህሎት ከማስጨበጥ ባሻገር አመለካከቱን፣ አስተሳሰቡን እና ስብዕናውንም ይቀርጻል። ትምህርት በሰዎች ውስጥ ፍቅርን፣ ሰብአዊነትን፣ አስተዋይነትን፣ ከራስ በላይ ለሌሎች ማሰብን፣ ያጎናጽፋል። ህግ አክባሪ፣ ስራ ወዳድ፣ ከእኩይ ስነምግባር የራቁ ዜጎች በትምህርት ቤት ይፈጠራሉ።

ሰዎች ከእድሜያቸው በአማካኝ አንድ ሶስተኛውን በትምህርት ቤት ያሳልፋሉ። የሰው ልጆች ተወልደው በአፍላ እድሜያቸው መጀመሪያ የሚረግጡት ማህበራዊ ተቋም ትምህርት ቤት ነው። ከመዋዕለ ህጻናት የሚጀምረው የሰው ልጆች እና የትምህርት ቤት ቁርኝት ከእድሜ ጋር አብሮ ከፍ እያለ የመጀመሪያ ደረጃ፣ መለስተኛ፣ ከፍተኛ እያለ ይዘልቃል። ኮሌጆች እና ዩኒቨርስቲዎች ተማሪዎች ሰፊ ወደ ሆነው የእውቀት ውቅያኖስ፣ የጥናት እና የምርምር ዓለም የሚሸጋገሩባቸው የተከበሩ የዕውቀት አጸዶች ናቸው። በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ሀገርንና ህዝብን የሚያገለግሉ ስብእናዎች በእነዚህ የትምህርት ማእከላት ያለፉ ናቸው። የሀገር መሪዎች፣ ሳይንቲስቶች፣ ጠቢባን፣ ሀኪሞች፣ ፖለቲከኞች፣ ወታደሮች፣ በሙሉ የትምህርት ቤት ምርቶች ናቸው።

ትምህርት በ21ኛው ክፍለ ዘመን

ባለንበት 21ኛው ክፍለ ዘመን ትምህርት ለሰው ልጆች ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ እድገት መሰረት እንደሆነ እሙን ነው። ባለንበት የሉላዊነት ዘመን የትምህርት እና የእውቀት አስፈላጊነት ከመቼውም ጊዜ በላይ ከፍ ብሏል። የትምህርት አስፈላጊነት እና ዋጋ በግለሰብ፣ በቤተሰብ፣ በሀገር እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በከፍተኛ ደረጃ አድጓል። ያደጉት ሀገራት ከዓመታዊ በጀታቸው ዳጎስ ያለ ሀብት ለትምህርት እና ለሰው ኃይል ልማት ይመድባሉ። እነዚህ ሀገራት በሰው ኃይል ልማት ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት በየትኛውም ዘርፍ ላይ ከሚፈስ መዋዕለ-ንዋይ እጅግ አዋጭ እና ለግለሰብ፣ ማህበረሰብ እና ለሀገር ዕድገት ተወዳዳሪ የሌለው አስተዋፅዖ ማድረግ የሚችል መሆኑን ጠንቅቀው ያውቃሉ። ይህን በማድረግም የእድገት ግስጋሴያቸው እንደጋለ እንዲቀጥል ለነጋቸው ዛሬ ጠንካራ መሰረትን ይጥላሉ።

ዓለም አቀፍ እና አህጉር አቀፍ

ስምምነቶች የትምህርትን አስፈላጊነት አበክረው ይዘክራሉ። የሚሊኒየሙ የልማት ግቦች፣ የዘላቂ ልማት ግቦች፣ የአፍሪካ፣ የአውሮፓ እና የአስያና ሌሎች አህጉራዊ ተቋማት ለትምህርት እና ስልጠና ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣሉ፤ ትምህርት የሰው ልጆች ህልውና፣ የዓለም ሰላም እና እድገት መሰረት እንደሆነ ይመሰክራሉ።

> የአለም ኢኮኖሚ ፈጣን የምርት እና ግብይት ስርአት የተመሰረተው፣ አንዱ ሀገር ከሌላው የተሻለ ተወዳዳሪ የሚሆነው እንደ ቀድሞው ሀገራት ባላቸው የተፈጥሮ ሀብት ክምችት፣ መሬት፣ ወንዝ፣ ነዳጅ ወይም ማእድን ሳይሆን በእውቀት እና ፈጠራ ነው።

በምጣኔ ሀብት ዘርፍ ሰፊ ተቀባይነት ካላቸው ጽንሰ ሀሳቦች አንዱ "እውቀት መር ኢኮኖሚ" (knowledge economy) ነው። የአለም ኢኮኖሚ ፈጣን የምርት እና ግብይት ስርአት የተመሰረተው፣ አንዱ ሀገር ከሌላው የተሻለ ተወዳዳሪ የሚሆነው እንደ ቀድሞው ሀገራት ባላቸው የተፈጥሮ ሀብት ክምችት፣ መሬት፣ ወንዝ፣ ነዳጅ ወይም ማእድን ሳይሆን በእውቀት እና ፈጠራ ነው። ባለፉት ጥቂት አስርት አመታት ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ያስመዘገቡ ሀገራትን ታሪክ እና የእድገታቸውን መሰረት ስንፈትሽ የእድገታቸው አንቀሳቀሽ ሞተር እውቀት፣ ክህሎት እና ምርምር ሆኖ እናገኘዋለን። የምስራቅ አስያ ሀገራት ጃፓን፣ ኮሪያ፣ ቻይና፣ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ናቸው።

ትምህርት በኢትዮጵያ

እውቀት እና ጥበብ በሀገራችን የረዥም ጊዜ ቁርኝት አላቸው። የረዥም ታሪክ ባለቤት የሆነቸው ኢትዮጵያ ከትምህርት ጋር የተዋወቀችው ማልዳ ነው። እንደ ዛሬው አለም ጥሎን ሳይነጉድ እውቀት ከሚቀሰምባቸው የዓለም ማእዘናት አንዷ ሀገራችን ኢትዮጵያ እንደነበረች ታሪክ ምስክር ነው። ቀደም ባሉት ዘመናት አብያተ ክርስቲያናት፣መስጊዶች፣ ገዳማት እና መድረሳዎች የትምህርት ማእከላት ሆነው አገልግለዋል። በእነዚህ ማእከላት ከመለኮታዊ ትምህርቶች ባሻገር ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፍ፣ ፍልስፍና፣ ሂሳብ፣ ስነ ፈለክ፣ ስነ ህይወት እና ሌሎች በርካታ የእውቀት ዘርፎች ትምህርት ይሰጣል። የአረብኛ እና እና የግእዝ ቋንቋዎች በሀገራችን የትምህርት ስርአት ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጾ እንደነበራቸው የሀገራችን ቱባ ዶሴዎች ህያው ምስክር ናቸው።

ለሺህ አመታት ከቆዩት ነባር እና ሀገር በቀል የትምህርት ማእከሎቻችን ጎን ለጎን፣ ዘመናዊ ትምህርት በ16ኛው ክፍለ ዘመን ከአውሮፓ ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ ይታመናል። ይሁን እንጂ ዘመናዊ ትምህርት በመንግስት እውቅና በይፋ የተጀመረው በ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ እንደሆነ የሀገራችን የትምህርት ታሪክ ይመሰክራል። ዘመናዊ ትምህርት በሀገራችን ሲጀምር የትምህርቱ ይዘት እና አብዛኛው መምህራን የውጭ ሀገር ዜጎች ነበሩ። በሀያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ በአዲስ አበባ እና በጥቂት ዋና ዋና ከተሞች የተጀመረው ዘመናዊ ትምህርት ቀስ በቀስ በሁሉም ክፍላተ-ሀገራት ተስፋፋ። ዛሬ ላይ በመላ ሀገሪቱ በሺህዎች የሚቆጠሩ ትምህርት ቤቶች ተፈጥረዋል።

ትምህርት እና ነጻነት

ትምህርትን አስመልክቶ ከላይ በደምሳሳው የተመለከቱትን የታሪክ፣ የንድፈ ሀሳብ እና የአለም ተሞክሮ በጥልቀት የተረዳው ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ለትምህርት፣ ለስልጠና እና ለሰው ኃይል ልማት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቷል። ነጻ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለሃገር እድገትና ልማት ወሳኝ ነው ብሎ ያምናል። ነጻ ትምህርት የአንድ ሀገር እና ህዝብ መሰረት፣ የሀገረ መንግስት ምሰሶ፣ የሀገር ህልውና ዋስትና ነው ብሎ ያምናል። ነጻ ሀገራችን ካለችበት እጅግ አሳሳቢ የእድገት ደረጃ ተላቃ ወደ አደጉት ሀገራት ክበብ ለመቀላቀል

> ያምናል። ነጻ ትምህርት የአንድ ሀገር እና ህዝብ መሰረት፣ የሀገረ መንግስት ምሰሶ፣ የሀገር ህልውና ዋስትና ነው ብሎ ያምናል።

የሚወስደው ብቸኛው መንገድ ትምህርት ነው ብሎ ያምናል። የተማረ የሰው ኃይል የሀገርን ውስን ሃብት በአግባቡ በመጠቀም ሀገራችን በኢንዱስትሪ እንድትገሰግስ፣ በሳይንስ እና ቴክኖሎጂ እንድትመነደግ፣ ግብርናችን ከበሬ ቀንበር ተላቆ በዘመናዊ መንገድ አርሰን፣ ወቅተን

ጎተራችን እንዲሞላ የተማረ የሰው ኃይል መተኪያ የሌለው ማሳሪያ ነው ብሎ ያምናል ነጻፓ። ኢትዮጵያን ጠፍንጎ ከያዛት ድህነት ለመውጣት አስተማማኝ እና አዋጩ መንገድ ትምህርት ነው።

> ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ሀገር ማለት በዋናነት ሰው ነው ብሎ ያምናል። ሰው ደግሞ ሰው የሚሆነው በትምህርት፣ በእውቀት እና በጥበብ ነው።

ነጻፓ ሰብአዊ መብቶችን የሚያከብር፣ ለሰው ልጅ ነጻነት እና እኩልነት ዘብ የሚቆም፣ ለፍትሕና ለሠላም መከበር የሚታገል፣ ለሀገርና ለህዝብ ፍቅር ያለው፣ በአካልና በሥነ-ምግባር የታነጸ፣ ሁለንተናዊ ስብዕና የተላበሰ ትውልድ የማፍራት ስራ ከትምህርት ቤት እንደሚጀምር ይገነዘባል። ፍትህን የሚያረጋግጥ፣ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን የሚጠየፍ የመንግስት ስርአት ለመገንባት የተማሩ፣ በእውቀት እና በአመለካከት የታነጹ ዜጎችን ማፍራት አማራጭ የሌለው መንገድ ነው ብሎም ያምናል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ሀገር ማለት በዋናነት ሰው ነው ብሎ ያምናል። ሰው ደግሞ ሰው የሚሆነው በትምህርት፣ በእውቀት እና በጥበብ ነው። የነጻፓ ሀገርን የማልማት እና የመለወጥ እሳቤ በዚህ ግልጽ እና ቀላል እንዲሁም ቦታ እና ዘመን በማይሽረው ሀቅ ላይ የተገነባው ነው። የሰው ልጆች የሩቅም ሆነ የቅርብ ጊዜ ታሪክ የሚያረጋግጠውም ይህንኑ ነው።

ትምህርት መር ብሄራዊ የልማት ስትራቴጂ

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ የትምህርትን ሁለንተናዊ ጥቅም ከጽንሰ ሀሳብ፣ ከዓለም ተሞክሮ እና ከተጨባጩ በመረዳት የሰው ኃይል ልማትን የፓርቲው የፖሊሲ ማጠንጠኛ፣ የፖሊሲ እና ስትራቴጂዎቹ መሰረት አድርጎ ፕሮግራሙን ገና ከማለዳው አሰናድቷል። ይህንን የፓርቲውን አቋም በገቢር ለማሳየት የፓርቲው ሀገር አቀፍ

የልማት እና የለውጥ ማእቀፍ “ትምህርት መር ብሄራዊ የልማት ስትራቴጂ” ብሎ ሰይሟል። በዚህም ትምህርት እና የሰው ኃይል ልማት የፓርቲው የፖሊሲ የጀርባ አጥንት መሆኑን በተጨባጭ አስመስክሯል። “ትምህርት መር ብሄራዊ የልማት ስትራቴጂ” የልማት እና የእድገት መሰረቱም ሆነ ውጤቱ ለሰው ልጆች ነው የሚል ጥልቅ ፍልስፍናዊ ይዘት እና አስተሳሰብ ሲሆን ማዕከሉ ሰው ነው።

ነእፓ የሀገራችንን ቁልፍ ችግሮች ለመፍታት ትምህርት መር ብሄራዊ የልማት ስትራቴጂ ፍቱን መፍትሄ ነው ብሎ የሚያምን ሲሆን በሚቀጥሉት ጥቂት አንቀጾች ይህ ስትራቴጂ የሀገራችንን ችግሮች ለመፍታ ያለውን ፋይዳ ዋና ዋና ዘርፎችን ማለትም ግብርና፣ ኢንደስትሪ፣ ማክሮ ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ እና መልካም አስተዳደር እንደ ማሳያ በመዳሰስ ቀርበዋል።

➢ የሀገራችን ግብርና እጅግ ኋላ ቀር ሲሆን አለም ከደረሰበት ብዙ ዘመን ወደ ኃላ ቀርቷል። የሀገራችን አርሶ አደር አብዛኛው ቅድመ አያቶቹ ሲጠቀሙበት በነበረን ማረሻ፣ ሞፈር፣ ቀምበር እና ወገል ይጠቀማል። ዝናብ ጠብቆ በእጁ ይዘራል፣ በማጭድ ይሰበስባል፣ አውድማ ላይ በበሬ ይወቃል። እድለኛ ከሆነ ለራሱ እና ለቤተሰቡ የአመት ቀለቡን ያመርታል። ካልሆነ እጁን ለእርዳታ ይዘረጋል። ግብርናችንን አዘምነን በምግብ ራሳችንን ለመቻል፣ በእውቀት የሚመራ፣ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ የፈጠራቸውን ዘመናዊ የእርሻ መሳሪያዎች፣ የተሻሻሉ የእርሻ እና የእንስሳት እርባታ ግብአቶች ልንጠቀም ይገባል። ማሳዎቻችን በበሬ፣ በሞፈር እና ቀንበር ምትክ በትራክተር፣ በኮምባይነር፣ እንዲሁም በሌሎች ዘመናዊ የእርሻ መሳሪያዎች ሊሞሉ ይገባል። ይህ ትምህርት እና እውቀት መር የግብርና ስትራቴጂን ይጠይቃል።

➢ የሀገራችን የኢንደስትሪ ዘርፍ እጅግ ደካማ ሲሆን፣ ብዙዎቹ የሀገራችን ፋብሪካዎች የጎጆ ኢንደስትሪ ከሚባለው እምብዛም ከፍ ያላሉ፣ የግብርና ውጤቶችን በማቀነባበር ላይ የተሰማሩ ናቸው። ገሚሶቹ ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ ከውጭ የመጡ ምርቶችን በመገጣጠም እና መጠነኛ እሴት በመጨመር በጥራትም ሆነ በብዛት ዝቅተኛ ምርት ያመርታሉ። በዚህም የሀገራችን የአምራች ኢንዱስትሪዎች ለሀገራዊ ኢኮኖሚ ያላቸው አስተዋጾ እጅግ አናሳ እንዲሆን አድርጎታል። የኢንዱስትሪ ዘርፋችን አሁን ካለበት እጅግ ኃላ ቀር ደረጃ ከፍ ለማድረግ በእውቀት ሊመራ፣ ዘመኑ ካፈራቸው የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ውጤቶች ተቋዳሽ እንዲሆን ማድረግ የሚያስፈልግ ሲሆን ይህም በዋናነት የሰለጠነ የሰው ኃይል ይፈልጋል። ይህም ትምህርት እና እውቀት መር የኢንዱስትሪ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ይጠይቃል።

➢ የሀገራችን ቁልፍ የማክሮ ኢኮኖሚ ችግሮች ተብለው ከሚጠቀሱት መካከል የዋጋ ግሽበት እና ስራ አጥነት በግንባር ቀደምትነት ይገኛሉ። በግብርናም ሆነ በኢንዱስትሪው መስክ በአመት የምናመርተው ምርት ከፍላጎት አንጻር ሲነጻጸር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። በመሆኑም የግብርና ምርቶችን ጨምሮ አብዛኛው ፍጆታችን ከውጭ በምናስመጣቸው ምርቶች ላይ የተመሰረተ ነው። በግብርናም ሆነ በኢንዱስትሪ መስክ የማምረት አቅማችን እጅግ አናሳ በመሆኑ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት የኢኮኖሚያችን መገለጫ ሆኗል። በዘላቂነት የዋጋ መረጋጋትን እውን ለማድረግ፣ በአገር ውስጥ በቂ ምርት ልናመርት የግድ ይላል። ይህ ደግሞ የሰለጠነ የሰው ኃይል ላይ የተንጠለጠለ ነው።

> **“ትምህርት መር ብሄራዊ የልማት ስትራቴጂ” የልማት እና የእድገት መሰረቱም ሆነ ውጤቱ ለሰው ልጆች ነው የሚል ጥልቅ ፍልስፍናዊ ይዘት እና አስተሳሰብ ሲሆን ማዕከሉ ሰው ነው።**

➢ ስራ አጥነት የሀገራችን ህዝቦች በአጠቃላይ በተለይም የወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ዋነኛ ተግዳሮት ነው። የዝናብ ጥገኛ በሆነ ግብርና እና ኋላ ቀር ኢንዱስትሪ ላይ የተመሰረተው ኢኮኖሚያችን በቂ የስራ እድል ሊፈጥር አልቻለም። ነእፓ ለዜጎች የስራ እድል መፍጠር ከፍተኛ ትኩረት ከሚሰጣቸው ዘርፎች አንዱ እና ቀዳሚው ሲሆን፣ ለዜጎች ስራ መፈጠር ያለውን ከፍተኛ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እንድምታ በጽኑ ይገነዘባል። ትምህርትን እና የሰው ኃይል ልማትን እንደ ቁልፍ ብሄራዊ የልማት ስልት የሚከተለው ነእፓ በሳይንስ እና ቴክኖሎጂ የታገዘ እና በእውቀት የሚመራ የስራ እድል ፈጠራ ፕሮግራሞችን ቀርጾ ተግባራዊ ያደርጋል። የነእፓ ትምህርት ተኮር የልማት ስትራቴጂ ሰራ ፈጣሪ ዜጎችን መፍጠር ዋና ባህሪው ነው።

➢ ከዚህ አንጻር ነእፓ ከተለመዱት የስራ መስኮች በተጨማሪ በአይነት እና በብዛት ሰፊ የስራ እድል ለመፍጠር የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ እና ዓለም አቀፍ መልካም ተሞክሮዎችን ታሳቢ ያደረገ የተቀናጀ የስራ ፈጠራ መርሀ ግብር ተግባራዊ ያደርጋል። የነእፓ የተቀናጀ የስራ ፈጠራ ፕሮግራም በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠ የሰው ኃይል በማፍራት የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን መሳብ እና በዚህም ሰፊ የስራ እድል መፍጠርን ያካትታል። ነእፓ ለዜጎች በሀገር ውስጥ የስራ እድል ከመፍጠር ባሻገር በሌሎች ሀገራት የተሻለ የስራ እድል የሚያገኙበት እና ለሀገራቸው የቴክኖሎጂ ሽግግር እድል የሚፈጥሩበት አሰራር ተግባራዊ ያደርጋል።

➢ በፖለቲካ ዘርፍ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ የዴሞክራሲ አላባውያን ጨቅላነት፣ ሰላም እና መረጋጋት አለመኖር፣ የመልካም አስተዳድር ሽታው መጥፋት፣ ነጻ እና ፍትሀዊ ምርጫ ስርአት እና ባህል አለመኖር፣ ደካማ ቢሮክራሲ፣ ደካማ የፖለቲካ ባህል፣ አቅመ ቢስ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ደካማ መንግስት የፖለቲካችን መገለጫዎች ናቸው። ለረዥም ዘመናት በፊውዳል ስርአት ሲተዳደር የቆየው ባላባታዊ ፖለቲካ ክፉኛ ተጠናውቶታል። የፖለቲካ ቅኝታችን ከሀሳብ ይልቅ ኃይል፣ ከብአር ይልቅ ብረት ይቀናዋል። የፖለቲካ አስተሳሰባችን ከአንድነት ይልቅ ልዩነት፣ ከመሰብሰብ ይልቅ መከፋፋል፣ ከፍቅር ይልቅ ጥላቻ፣ ከመተጋገዝ መወጋገዝ፣ ከመተማመን መጠራጠር ዋነኛ መገለጫዎቹ ናቸው። ፖለቲካችን በእውቀት እና በስሌት ሳይሆን በስሜት የሚመራ ነው። ከዚህ የውድቀት እና የቀውስ አዙሪት ለመውጣት፣ አሮጌውን የፖለቲካ፣ የአስተዳደር፣ የዴሞክራሲ እና የፍትህ ስርአታችንን ለመቀየር በእውቀት፣ በክለሳት እና በስነምግባር የታነጸ አዲስ ትውልድ መገንባት ያስፈልጋል።

ትምህርት መር የልማት ስትራቴጂ እነዚህ እና ሌሎች የሀገራችን ቁልፍ የልማት ችግሮችን በአስተማማኝ መልኩ ለመቅረፍ በጉድፈ ሀሳብ የተደገፈ እና በተግባር የተረጋገጠ የፖሊሲ መሳሪያ ነው። ነእፓ ይህንን ስትራቴጂ በመጠቀም የሀገራችንን ማህበረ-ኢኮኖሚ እና ፖለቲካዊ ችግሮች ለመፍታት “ትምህርት መር ብሄራዊ የልማት ስትራቴጂ” ነድፎ ለኢትዮጵያ ህዝብ ያቀረበ ሲሆን ፓርቲው በምርጫ አሸንፎ ሀገር የመምራት እድል ሲያገኝ ይህንኑ ፖሊሲ ወደ ተግባራዊ በማድረግ ኢትዮጵያን አንቀው ከያዟት ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለማላቀቅ ይሰራል።

የነእፓ ትምህርት መር የለውጥ ፕሮግራም እና ተራማጅ የፖለቲካ አስተሳሰብ፣ ሀገራችንን ካለችበት ዘርፈ ብዙ እና ውስብስብ ችግሮች በአጭር ጊዜ አላቆ ከአለም ታላላቅ ሀገራት መካከል ለማሰለፍ ፓርቲው ያለውን ውጥን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። ፓርቲው ለትምህርት እና ለእውቀት የሰጠው ከፍተኛ ቦታ ምናልባትም በአለም ደረጃ አጠቃላይ የለውጥ እና የልማት አጀንዳውን በትምህርት እና የሰው ኃይል ልማት ላይ የገነባ ብቸኛ የፖለቲካ ፓርቲ ያደርገዋል።

●●●

የስድስተኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ስድስት ተሞክሮዎች

ስድስተኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ሰኔ 14 2013 እና መስከረም 20 2014 ተካሂዷል። ምርጫው ከዚህ ቀደም ከተካሄዱ አምስት ምርጫዎች አኳያ ሲታይ በአንጻራዊነት ሰላማዊ እንደነበር በርካቶች የሚስማሙ ቢሆንም ብዙዎች እንደጠበቁት ነጻ እና ዴሞክራሲያዊ እንዳልነበር መራጮች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ታዛቢዎች መስክረዋል።

ኢትዮጵያ የፖለቲካ ሽግግር ውስጥ ባለችበት ወቅት የተካሄደው ምርጫ፣ በበርካታ የሰላም መደፍረስ፣ የመልካም አስተዳደር እጦት እና ሌሎች ማህበራዊ እና ኢኮኖሚ ችግሮች የታጀበ ነበር። በሰሜኑ የሀገሪቱን ክፍል ሲካሄድ የነበረው ጦርነት እና ጦርነቱ በዜጎች ስነ ልቦና ላይ የፈጠረው ጫና፣ በየአካባቢው ያሉ ግጭቶች፣ ከምርጫው ቀደም ሲል የአንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች አመራሮች መታሰር፣ ታዋቂ ግለሰቦች ግድያ፣ የኮሮና ወረርሽኝ ከብዙ በጥቂቱ የሚጠቀሱ ተግዳሮቶች ነበሩ።

ምርጫው ከዚህ በፊት ከተካሄዱት ምርጫዎች አንጻር ሲታይ ቀላል የማይባሉ መሻሻሎች የታዩበት መሆኑ የማይካድ ሲሆን፣ ልዩ ልዩ የፖለቲካ፣ የሎጂስቲክ፣ አስተዳደራዊ እና ቴክኒካዊ ችግሮች እንደነበሩበት ግን መካድ አይቻልም። በዚህ አጭር ጽሁፍ የስድስተኛውን ሀገር አቀፍ ምርጫ ሂደት እና ተሞክሮዎች ለመዳሰስ የተሞከረ ሲሆን፣ ዓላማው ከምርጫው እንደ ሀገር የወሰድናቸውን ትምህርቶች ተጠቅመን ቀጣይ ምርጫዎችን የተሻለ ለማድረግ ጥቆማ መስጠት ነው። በዚህ መሰረት በስድስተኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ከተገኙ ልምዶች መካከል ስድስቱ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

i. የፓርቲ እና መንግስት መቀላቀል

ከሀገራችን ፖለቲካ ቁልፍ ችግሮች መካከል አንዱ የመንግስት እና የፓርቲ መቀላቀል ነው። ባለፉት 30 ዓመታት ሀገሪቱን ሲያስተዳድር የነበረው አውራ ፓርቲ በፓርቲ እና በመንግስት መካከል ሊኖር የሚገባውን ድንበር አፍርሶ የመንግስት መዋቅርን የፓርቲ አጀንዳ ማስፈጸሚያ አድርጎ ሲጠቀምበት ቆይቷል። ይህ አሰራር ባለፉት የተሀድሶ አመታትም ሊስተካከል አልቻለም።

> ፓርቲ እና መንግስት አንድም ሁለትም በሆኑባት ሀገር የተካሄደው 6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ፣ አንዳንድ የገዢው ፓርቲ አመራሮች የምርጫውን ሂደት ለማዛባት ምቹ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል።

ፓርቲ እና መንግስት አንድም ሁለትም በሆኑባት ሀገር የተካሄደው 6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ፣ አንዳንድ የገዢው ፓርቲ አመራሮች የምርጫውን ሂደት ለማዛባት ምቹ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል። በተለይ በወረዳና እና በከተማ ደረጃ ያሉ የመንግስት አመራር አካላት በምርጫው ሂደት ላይ ከፍተኛ ጫና ለማሳደር ሲሞክሩ መታየታቸው መራጩ ህዝብ እና ምርጫውን በቅርብ ሲከታተሉ የነበሩ አካላት ታዝበዋል።

ተፎካካሪ ፓርቲዎች በነፃነት መቀስቀስ እንዳይችሉ ማድረግ፣ የመራጮች ምዝገባ ሂደት ውስጥ ጣልቃ መግባት፣ የመንግሥትን ሀብት በተለይ ተሽከርካሪዎችን ለምርጫ ቅስቀሳ ስራ መጠቀም፣ የመንግሥት ሚዲያ ተቋማት ለገዢው ፓርቲ የተሻለ የሚዲያ ሽፋን መስጠት ከዚህ አንጻር ከታዩ ችግሮች ማሳያ ናቸው። በቀጣይ የሚካሄዱ ምርጫዎች ነጻ እና ፍትሀዊ ይሆኑ ዘንድ የመንግስት መዋቅርን ከፓርቲ መዋቅር መነጠል እጅግ አስፈላጊ ነው።

ii. በተፎካካሪ ፓርቲዎች መካከል በትብብር አለመስራት፣

ገዢው ፓርቲ አብላጫ ድምጽ እንዲያገኝ ካደረጉ ምክንያቶች አንዱ የተፎካካሪ ፓርቲዎች ተቀናጅተው አለመስራት አንዱ ነው። የፖለቲካ ፓርቲዎች በአዲሱ አዋጅ

1162/2011 ዳግም በተመዘገቡበት ማግስት በተካሄደው ምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥምረት/ቅንጅት ወይም ግንባር ፈጠረው በምርጫው ለመሳተፍ አልቻሉም። በዚህም ምክንያት ከፍተኛ የመራጮች ድምጽ መከፋፈል እና ብክነት ተከስቷል።

ባለፉት ሶስት አመታት በርካታ አዳዲስ ፓርቲዎች የተቋቋሙ ሲሆን፣ ተቀራርቦ ለመስራት የጊዜ ውስንነት እንደ ምክንያት ቢጠቀስም፣ በፓርቲዎች መካከል ተቀራርቦ የመስራት ደካማ ባህላችን ለችግሩ ዋነኛው ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። በፓርቲዎች መካከል የጠፋው የመተማመን ባህል፣ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለራሳቸው የሰጡት የተጋነነ ግምት፣ በምርጫ ወቅት ቅንጅት ለመፈጠር የሚቻልበት አሰራር እና ህጋዊ የጊዜ ገደብ ወዘተ በስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ በተፎካካሪ ፓርቲዎች መካከል ጠንካራ ቅንጅት እንዳይፈጠር አስተዋጾ አድርጓል። በምርጫው የተስተዋለውን የድምጽ መከፋፈል ለማስቀረት በተፎካካሪ ፓርቲዎች መካከል በቅንጅት መስራት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

> በምርጫው የተስተዋለውን የድምጽ መከፋፈል ለማስቀረት በተፎካካሪ ፓርቲዎች መካከል በቅንጅት መስራት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

በሀገራችን የምርጫ ታሪክ ምርጫ 1997፣ ተፎካካሪ ፓርቲዎች የፈጠሩት ቅንጅት ያስገኘው ውጤት በስፋት የሚታወስ ቢሆንም፣ ይህንን ተሞክሮ ለማስቀጠል በቀጣይ በሚካሄዱ ምርጫዎች ተፎካካሪ ፓርቲዎች ተቀራርበው ሊሰሩ ይገባል።

iii. የምርጫ ስርዓት ለውጥ

በህገ መንግስቱ በተደነገገው መሰረት የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ የአብላጫ ድምጽ (First Past the Post) ስርዓት ነው። ይህ የምርጫ ስርአት በአንድ የምርጫ ክልል ከሚወዳደሩ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩዎች መካከል የተሻለ ድምጽ ያገኘውን አሸናፊ የሚያደርግ ነው። በዚህ የምርጫ ስርዓት ተፍካካሪ ፓርቲዎች በተሸነፉበት የምርጫ ክልል የሚያገኙት ድምጽ ጥቅም አይኖረውም። ይህ የምርጫ ስርአት ለአተገባበር ቀላል መሆኑ ከሌሎች የምርጫ ስርዓቶች ተመራጭ ቢያደርገውም የመራጮችን ድምጽ በማባከን እንዲሁም የተለያየ ፖሊሲ እና የፖለቲካ አጀንዳ ያላቸው የፖለቲካ ኃይሎች በፓርላማ የመወከል እድላቸውን ያጠባል። እንደ ኢትዮጵያ የብሄር፣ የባህል፣ የእምነት ወዘተ ብዝሀነት ባለባቸው ሀገራት የአብላጫ የምርጫ ስርአት አይመከርም። ይህንን የምርጫ ስርአት ለመቀየር ከምርጫ በፊት የተለያዩ ውይይቶች ሲደረጉ የቆዩ ቢሆንም፣ የምርጫ ስርዓቱን መቀየር ግን አልተቻለም። ለዚህም ዋነኛው ምክንያት የምርጫ ስርዓቱን መቀየር ህገ መንግስታዊ ማሻሻያ የሚያስፈልገው መሆኑ ነው።

> በቀጣይ በሚደረግ የህገ መንግስት ማሻሻያ ስራ፣ ቅድሚያ ሊሰጣቸው ከሚገባቸው ድንጋጌዎች አንዱ የምርጫ ስርዓቱን አሁን ካለው ወደ ተመጣጣኝ የምርጫ ስርአት መቀየር ነው።

ይህንን የድምጽ መባከን በመቅረፍ፣ የተፎካካሪ እጩዎችን የማለፍ እድል ከፍ ለማድረግ፣ የምርጫ ስርዓቱን ወደ ተመጣጣኝ የምርጫ ስርአት (Proportional) መቀየር ያስፈልጋል። ተመጣጣኝ የምርጫ ስርአት ተፎካካሪዎች በየምርጫ ክልሉ የሚያገኙትን ድምጽ በመደምር እጩዎች የሚያገኙት ጠቅላላ ድምጽ ከጠቅላላው የመራጭ ቁጥር አንጻር ተመጣጣኝ የሆነ ወንበር የሚያገኙበትን እድል ይፈጥራል። ይህ አሰራር የድምጽ መባከንን የሚያስቀር ሲሆን፣ የተለያየ የፖለቲካ ፍላጎት ያላቸው መራጮች ድምጻቸው በህግ አውጪው ውስጥ እንዲወከል እድል ይሰጣል። በቀጣይ በሚደረግ የህገ መንግስት ማሻሻያ ስራ፣ ቅድሚያ ሊሰጣቸው ከሚገባቸው ድንጋጌዎች አንዱ የምርጫ ስርዓቱን አሁን ካለው ወደ ተመጣጣኝ የምርጫ ስርአት መቀየር ነው።

iv. የምርጫ አስፈጻሚዎች ገለልተኝነት

ለአንድ ምርጫ ተአማኒነት እና ለውጤቱ ቅቡልነት የምርጫ አስፈጻሚዎች ገለልተኝነት ቁልፍ ሚና ይጫወታል። በ6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ከተስተዋሉ ተግዳሮቶች መካከል በአንዳንድ አካባቢዎች የታዩ የምርጫ አፈጻሚዎች ወገንተኝነት አንዱ ነው። ችግሩን ለመቅረፍ በተለይም በምርጫ ቦርድ በኩል የተሻለ አሰራር ለመዘርጋት ሙከራ ቢደረግም ችግሩን ማስቀረት አልተቻለም። አንዳንድ የምርጫ አስፈጻሚዎች የገዢውን ፓርቲ እና የተፎካካሪ ፓርቲዎችን እጩዎች በእኩል ለማስተናገድ ያሳዩት ዳተኝነት በምርጫው ሂደት እና ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል። ቀጣይ ምርጫዎችን የተሻለ ለማድረግ የምርጫ አስፈጻሚዎችን አቅም መገንባት እና ከፓርቲ ወገንተኝነት ነጻ እንዲሆኑ ለማድርግ የተቀናጀ ስራ መስራት ያስፈልጋል።

v. ሁሉን አቀፍ ብሄራዊ መግባባት

በሀገራችን ለረዥም ጊዜ የቆዩ ዘርፈ ብዙ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሱ ዛሬ ላይ ደርሰናል። ብሄረ መንግስት ግንባታን ጨምሮ ብዛት ባላቸው ታሪካዊ እና ወቅታዊ አጀንዳዎች ዙሪያ ሰፊ እና የከረረ ልዩነት አለ። ችግሮቻችን በአመጽ እና በአፈሙዝ ለመፍታት ከሞመከር ባሻገር በውይይት እና በመግባባት ለመፍታት በሀገር ደረጃ የተደረገ አንዳች ሙከራ የለም። በተለያየ ጊዜ ኢትዮጵያን ያስተዳደሩ መንግስታት ቀድሞ የነበረውን ስርአት ሙሉ ለሙሉ በመቀየር እና የራሳቸውን ርዕዮተ ዓለም በኃይል በመጫን ሀገር ሲገዙ ኖረው አልፈዋል።

ከ6ኛው ጠቅላላ ምርጫ በፊት ከሚጠበቁ ቁልፍ የፖለቲካ ስራዎች ብሄራዊ መግባባት አንዱ ነበር። የተለያዩ አካላት በተወሰኑ ቅድመ ምርጫ አጀንዳዎች ላይ ድርድር እንዲደረግ ተደጋጋሚ ጥያቄ ያቀረቡ ቢሆንም ብሄራዊ መግባባት ሳይደረግ ምርጫው መካሄዱ በምርጫው ላይ አሉታዊ ተጽኖ አሳድሯል። የሀገራችንን የፖለቲካ ትኩሳት ከመሰረቱ ለማብረድ እና ሀገራዊ የምርጫ ታሪካችንን ይበልጥ ነጻ፣ ፍትሀዊ፣ ዴሞክራሲያዊ እና ሰላማዊ ለማድረግ ሁሉን አቀፍ ብሄራዊ ውይይት ማድረግ ይደር የሚባል ጉዳይ አይደለም።

vi. የህዝብ ቆጠራ

ህገ መንግስቱ የህዝብ ቆጠራ በየአስር አመቱ መደረግ እንዳለበት ይደነግጋል። የህዝብ ቆጣራ ማድረግ በእውነተኛ በመረጃ ላይ የተመሰረቱ ብሄራዊ እቅዶችን ለማዘጋጀት ብሎም የዜጎችን ፍትህዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ይረዳል። ወቅታዊና የተሟላ የስነ ህዝብ መረጃ መኖር ግድ ከሚሆንባቸው ሀገራዊ ጉዳዮች አንዱ ምርጫ ነው። ግልጽ፣ ነጻ እና ተአማኒ ምርጫን በአግባቡ ለማቀድ እና ለመተግበር የስነ ህዝብ መረጃ እጅግ አስፈላጊ ነው።

በሀገራችን የህዝብ ቆጠራ ከተካሄደ በህግ የተቀመጠው ጊዜ ያለፈ ሲሆን ቆጠራውን ለማካሄድ ታስቦ ከአንድም ሁለቴ ሳይሳካ ቀርቷል። በቂ እና ወቅታዊ የስነ ህዝብ መረጃ አለመኖር በስድስተኛው ሀገራዊ ምርጫ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽኖ ማሳደሩን ብዙዎች ይስማማሉ። ወቅታዊ የስነ ህዝብ መረጃ መኖር የምርጫ ክልሎችን ለማሻሻል፣ የምርጫ ቁሳቁስ ዝግጅት እና ስርጭትን እንዲሁም ሀብትን በአግባቡ ለመጠቀም ያግዛል። ቀጣይ ምርጫዎችን በተሻለ ሁኔታ ለማቀድ እና ለመተግበር ዘመኑ በደረሰበት ቴክኖሎጂ እና ባለሙያ የተደራጀ የስነ ህዝብ መረጃ የሚያስፈልግ ሲሆን ለዚህም የህዝብ ቆጠራ ማካሄድ ያስፈልጋል።

●●●

ከማኒፌስቷችን፡

ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስር

በቴክኖሎጂ ታግዞ በፍጥነት በማደግ ላይ ባለው ዓለም ዓቀፍ የኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ንቁ ተዋናይ እና ተወዳዳሪ ለመሆን ሀገራት አካባቢያዊ እና ዓለማቀፋዊ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ እና ማህበራዊ ትስስሮችን እንዲፈጥሩ አስገድዷል። ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ የአፍሪካ ሀገራት በዚህ እጅግ ፈጣን እና ተለዋዋጭ ዓለማቀፍ የንግድ እና የኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ እና የዜጎቻቸውን ኑሮ ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት እንዲያደርጉ አስገድዷል።

ከኢትዮጵያ የመልከዓ-ምድር አቀማመጥ፣ የህዝብ ብዛት፣ ወደብ-አልባነት እና ካላት የኢኮኖሚ መዋቅር አንጻር ሁሉን አቀፍ ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስር እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በጽኑ ያምናል። ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስር ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ብሎም ጂኦ-ፖለቲካዊ ፋይዳ እንዳለው የበርካታ የአውሮፓ፣ እስያ እና አፍሪካ ሀገሮች ተጨባጭ ተሞክሮ ያሳያል። ቀጠናዊ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ትስስር አገራት የሸቀጥ፣ የአገልግሎት፣ የካፒታል እና የሰው ኃይል እንቅስቃሴን የሚገድቡ አሰራሮችን እንዲያስወግዱ ያስችላል። እነዚህ እንቅፋቶች በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ ሃገራት የኢኮኖሚ እድገት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራሉ።

> ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስር ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ብሎም ጂኦ-ፖለቲካዊ ፋይዳ እንዳለው የበርካታ የአውሮፓ፣ እስያ እና አፍሪካ ሀገሮች ተጨባጭ ተሞክሮ ያሳያል።



ስኬታማና ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስር ሀገራት ያለባቸውን የመሰረተ-ልማት እና የካፒታል ውስንነት እንዲሁም የፖሊሲ እንቅፋቶችን በመቅረፍ በአባል አገራት መካከል የንግድ፣ የካፒታል፣ የሰው ሀብት እና የቴክኖሎጂ ፍሰትን በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ ያግዛል። እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ወደብ አልባ እና ትልቅ የህዝብ ቁጥር ላላቸው ታዳጊ አገራት፣ ሁሉን አቀፍ ቀጠናዊ ብሎም አህጉራዊ የኢኮኖሚ ትስስር እምቅ የኢኮኖሚ አቅማቸውን ለመጠቀም ላቅ ያለ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ፋይዳ አለው። ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስር ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ የአፍሪካ አገራት ያለባቸውን የኢኮኖሚ አቅም ውስንነት በመቅረፍ በአለም አቀፍ ገበያ ውስጥ ያላቸው ሚና ከፍ እንዲል ትልቅ የፖሊሲ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል። የኢትዮጵያ አምራች ድርጅቶች ዓለም ዓቀፍ ተወዳዳሪነት እጅግ ዝቅተኛ ሲሆን በአለም አቀፍ እና ቀጠናዊ የእሴት ሰንሰለት (Value chain) ጠንካራ ተሳትፎ የላቸውም።

ምንም እንኳ ኢትዮጵያ በተለያዩ ቀጣናዊ

የኢኮኖሚ ማህበረሰቦች (የምስራቃዊና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ COMESA እና የምስራቅ አፍሪካ በይነ-መንግስት IGAD) አባል ብትሆንም በብዙዎቹ ቀጣናዊ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ያላት ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ውስን ነው። ለምሳሌ በአሁኑ ጊዜ

> ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስርን ማጠናከር ለሀገራችን ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ትሩፋቶችን እንደሚያስገኝ በጽኑ ያምናል።

የምስራቃዊና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ (COMESA) ነጻ የንግድ ቀጠና ደረጃ ላይ ቢደርስም ኢትዮጵያ እስከ አሁን ይህንን ነጻ የንግድ ቀጠና አልተቀላቀለችም። በተመሳሳይ ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ ከ2003 ጀምሮ የአለም የንግድ ድርጅት (WTO) አባል ለመሆን ብታመለክትም እስከ አሁን የአባልነት ሁኔታዎችን ማሟላት ባለመቻሏ የድርጅቱ አባል መሆን አልቻለችም።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስርን ማጠናከር ለሀገራችን ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ትሩፋቶችን እንደሚያስገኝ በጽኑ ያምናል። ፈጣን እና የተሳለጠ የውጭ ንግድ እንዲሁም ቀልጣፋ የገበያ ስርአት፣ የላቀ አለም አቀፋዊ እና ቀጠናዊ ተወዳዳሪነት፣ ከፍተኛ የውጭ ቀጥተኛ መዋዕለ-ነዋይ (FDI) ፍሰት፣ መዋቅራዊ ሽግግርን በአጭር ጊዜ ማረጋገጥ፣ አካታችና ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት፣ ሰፊ የስራ እድል መፍጠር፣ ፈጣን ድህነት ቅነሳ፣ የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ ማሻሻል፣ ቀልጣፋ የንግድ ልውውጥ እና የካፒታል ፍሰት ከብዙ በጥቂቱ ሊጠቀሱ ይችላሉ። ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስር ካለው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ በተጨማሪ ሰላም ለራቀው እና የግጭት አውድማ ለሆነው የአፍሪካ ቀንድ ሰላምና መረጋጋትን ለማረጋገጥ ይረዳል። የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት እና የባህል ትስስር የአካባቢያዊ ቁርኝት ሌላው ጠቀሜታ ነው።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ሀገራዊ የልማት ራእዩን እውን ለማድረግ ከሚከተለው የምጣኔ ሀብት እና የማህበራዊ ፖሊሲዎች ጎን ለጎን ከጎረቤት ሀገራት እና ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ጋር ጠንካራ የኢኮኖሚ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ያደርጋል። ከጎረቤት ሀገራት እና ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ጋር የሚፈጠረው ቀጠናዊ የገበያ እና የኢኮኖሚ ትስስር በኢትዮጵያና በአካባቢው ሀገራት መካከል መንገድን ጨምሮ ሌሎች የመሰረተ ልማቶች፣ የንግድ ህጎች እና ቀጠናዊ ተቋማት ግንባታን ያፋጥናል።

ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ጠንካራና ሁሉን አቀፍ ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስርን ለመፍጠር ልዩ ልዩ አስቻይ ሁኔታዎችን የሚፈጥር ሲሆን ከእነዚህ መካከል የንግድ እና መዋዕለ-ነዋይ ዝውውር ለማቀናበር የሚያስችሉ ፖሊሲና አሰራሮችን ይቀርጻል፣ የትራንስፖርት፣ ኢንፎርሜሽ ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ እና የኢነርጂ መሠረተ ልማት ፕሮግራሞች ከጎረቤት ሀገሮች ጋር በቅንጅት እንዲነደፉ እና እንዲዘረጉ ያደርጋል፣ የሀገራችን የማክሮ ኢኮኖሚ እና የፋይናንስ ፖሊሲ የአፍሪካ እና አለም አቀፍ የፖሊሲ ማእቀፎችን ታሳቢ ባደረገ ሁኔታ እንዲከለሱ ያደርጋል፣ የተፈጥሮ ሀብቶች እንዲሁም ትምህርት እና ጤናን ጨምሮ ልዩ ልዩ ማህበራዊ አገልግሎቶች የአፍሪካ ህብረት እና ሌሎች ቀጠናዊ ድርጅቶች ካወጧቸው መስፈርቶች ጋር የተዋጁ እንዲሆኑ ያደርጋል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ሀገራችን እስከ ዛሬ በነበራት ተሞክሮ በአካባቢያዊ የኢኮኖሚ ትስስር ውጤታማ እንዳትሆን የሚያድጉ አሰራሮችን በመለየት በተሻለ አሰራር እንዲለወጡ ያደርጋል፣ የእርምት እርምጃዎችንም ይወስዳል።

> ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስር ካለው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ በተጨማሪ ሰላም ለራቀው እና የግጭት አውድማ ለሆነው የአፍሪካ ቀንድ ሰላምና መረጋጋትን ለማረጋገጥ ይረዳል።

በርካታ የአፍሪካ ሀገራት በተለያዩ የኢኮኖሚ ማህበረሰቦች ውስጥ አባል መሆን የአፍሪካን የኢኮኖሚ ትስስር እንዲጓተት ካደረጉ ምክንያቶች መካከል አንዱ ሲሆን ኢትዮጵያም የዚህ የተሳሳተ አሰራር ሰለባ መሆኗ ይታወቃል። ይህ ተደራራቢ አባልነት (Overlapping membership) የሀገራችን ፖሊሲ የመተግበር አቅምና ከኢኮኖሚ ትስስሩ የሚያገኙትን ጥቅም ይገድባል። በመሆኑም ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ ከተመሰረቱ የኢኮኖሚ ስብስቦች የተሻለ ተጠቃሚ በሚያደርጋት ውስጥ ብቻ እንድትወሰን ይደረጋል።

ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ትስስር አሸናፊዎች እና ተሸናፊዎችን (Winners and Losers) እንደሚፈጥር ይታወቃል። ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ ሀገራችን ከአካባቢው ሀገሮች ጋር በምትፈጥረው ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ትስስር በየትኛውም ሀገር ላይ ሊደርስ የሚችልን ጉዳት በመቀነስ ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርግ አሰራር እንዲፈጠር ይጥራል።

ሀገራችን ካላት ሰፊ እና እምቅ የተፈጥሮ ሀብት፣ ቁጥሩ ከፍተኛ የሰው ሀብት፣ ሰፊ የቆዳ ስፋት እና በአፍሪካ ቀንድ ካላት አማካኝ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ አንጻር ከአካባቢያዊ የኢኮኖሚ ትስስር ከፍተኛ ተጠቃሚ እንደምትሆን ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ በጽኑ ያምናል። ይህንን ታሳቢ በማድረግ ኢትዮጵያ የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጠና (AfCFTA) ብሎም የአለም የንግድ ድርጅትን እንድትቀላቀል ነእፓ አጥብቆ ይሰራል።